# አባቱን ገዳይ

(ሁማም) ገና ጨቅላ ሳለ በአስራ ሁለት ዓመቱ ነው አባቱ በሞት የተለየው። የቲሙን ትርፍራፊ ምግብና አሳቂ ልብስ ልታመጣለትና የሚኖሩባትን የጎስቋላዋን ክፍል ኪራይ የሚሆን ገንዘብ ለማግኘት በጎረቤት የምትሰራው እናቱ ናት የቲሙን ሁማም ያሳደገችው።

የጎረቤት ሥራ ያጎሳቆላት እናቱ በሳንባ መቆሸሽ በሽታ ተለክፋ ከአልጋ ላይ ዋለች። የእለት ጉርስ ስታጣ ወደ መንግስት ሆስፒታል ተጠግታ መታከም ጀመረች። መንግስት ሆስፒታል የምትበላውና የምትጠጣው፣የሚንከባከባት ሀኪም ታገኝ እንጂ በሽታውን ግን መቋቋም አልቻለችም።ትንሹን ልጇን እስከመጨረሻ ልትለየው መሆኑን ስታስብ ደግሞ ሀዘኑ በሽታዋን በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ አደረገው። በአንድ ጊዜ ሁለት ህመሞችን ማስታመም ጀመረች።አንደኛው ሰውነቷን የሚያደቀው በሽታ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሀሳቧን የሚንጠው ትካዜ ነበር።

እናቱ እስከ ወዲያኛው ስታሽልብ ልጅ ግን የነገ ተስፋውን ያጣ የምድር ነዋሪ የመሆን እጣ ፈንታ ደረሰው።ለመኖር

መብላት፣ለመብላትመስራት የግድ ነውና በርካሽ ክፍያ የግንበኝነት ሥራ ጀመረ፡፡ትምህርት ለመተው ተገደደ፡፡ ቀስ በቀስ ብቃት ያለው ግንበኛ ለመሆን በመቻሉ የኑሮ ሁኔታው ተሻሽሎ ጥሩ ነዋሪ መሆን ችሏል፡፡

ሁማም ግማሽ ዲኑን በጋብቻ ለማሟላት አስቦ ወደ ግንበኝነት መምህሩ የልጅህ ዳርልኝ ጥያቄ አንግቦ ተጓዘ፡፡ የልጂቱ አባት አላንገራገረም ጥያቄውን ተቀበለው፡፡ ዓመታት እየተተካኩ በሄዱ ቁጥር ሁማም ባለትዳርና የልጆች አባት ከመሆኑ ባሻገር በታማኝነቱ በጥራቱ እየታወቀ ዝናው እየተንሰራፋ መጣ፡፡ ይህ ዝናው ደንበኞቹን ያበዛለት ሲሆን በሥራ ከመወጠሩ የተነሳ በሳምንት ውስጥ የሚያርፍበት ቀን አልነበረውም፡፡ በየሁለት ዓመቱየሚጨምረው የቤተሰቡ አባላት ቁጥር ሌት ቀን እንዲሰራ ግድ ይለዋል (ሁማም) ለትምህርት ትኩረት ሰጥቶ ልጆቹን በጥራት ያስተማረ ሲሆን ‹‹እኔ በህይወት ውስጥ ብዙ ተሰቃይቻለሁ እናንተ ግን በህይወት እያለሁም ሆነ ከአረፍኩ በኋላ ማረፍ አለባችሁ›› የሚለውን ቃሉን ሁል ጊዜ ለሚስቱና ለልጆቹ ይደጋግመው ነበር፡፡ የበኩር ልጁ ከዩንቨርስቲ ተመርቆ ሥራ ሲይዝ ሁማም ሀምሳ ዓመት ቢቃረበውም በሙያው ተሰማርቶ ማሰራቱን አልተወውም፡፡ ሰውነቱ በተዳከመ ቁጥር የደንበኞቹ ቁጥር እየተበረከተ ነበር የሚመጣው፡፡

የበኩር ልጁ አንዲት የዩንቨርስቲ አቻው ጋር ትዳር ሊመሰርት ጥያቄ ቢያቀርብም የቀረበለት ቅድመ ሁኔታ ከበድ ያለ ነበር። ከቤተሰቦቹ ተለይቶ ጎጆ ሊወጣ፤ የሀብታም ልጅ እንደመሆኗ መጠን ለእርሷ የሚስማማት ቤት ሊከራይ፤ውድና ውብ በሆነ የቤት እቃዎችን ሊያሟላ፣አዲስ መኪና ሊገዛለት ነበር። በፍቅር ልቡ የታወረው ወጣት አለምንም ማመንታት ነበር ቅድመ ሁኔታውን የተቀበለው። ከዚያን ቀን ጀምሮ የሁማም የበኩር ልጅ ብድርና የቤት ወጪ ትከሻውን ተጭኖት በሀሳብና በጭንቀት ስር መዋተት ጀመረ። አባት የልጁ ሁኔታ ቢያስጨንቀውም ቤቱን በማሳደር፤ በዩንቨርስቲ እየተማሩ ያሉ ልጁን በማስተማር ተወጥሮ ነበርና ምንም ሊረዳው አልቻለም።

ዩንቨርስቲ ምሩቅ ሚስቱ ደመወዝ፤ ለልብስ፣ለጌጥና ለመዝናኛ ፕሮግራሞች ከምታወጣቸው የግል ውጪ አያልፍም። አንድ አንዴ ለግል ወጭ ስለማይበቃት ከባሏ ተጨማሪ ወጪ ትጠይቃለች።

ሁማም ልጁን ለመርዳት አቅሙ ባይፈቅድም ልጁ ከሚሰራበት ሚኒስተር መስሪያ ቤት በረጅም ጊዜ ክፍያ ያገኘው ቁራጭ መሬት ላይ ቤት በመስራትና ግንባታውን ወጪ በመሸፈን ሊረዳው ፈልጓል። ነገር ግን ግንባታውን ካጠናቀቀ በኋላ ሁማም አብሮት ሊኖረው በቅድመ ሁኔታው

ተስማምተው በሁለት ዓመት ውስጥ ግንባታውን አጠናቀቀ። በሁለት ወር የሚያልቅ ቤት ሁለት ዓመት የፈጀበት የእለት ሥራውን ሲያጠናቅቅና የእረፍት ቀኑን (ጁመአን) በመጠቀም ስለገነባው ነው።ይህንንም የሚያደርገውስቤቱ ግንባት ወጪየሚሆን ለመሰባሰብ ነበር ቤቱን በመገንባት ሂደት ላይ አጋዥ ግንበኞቹ ያለምንም ክፍያ ለመምህራቸው ክብር ሲሉ ያበረከቱት አስተዋጽኦ ቀላል አልነበረም።የቤቱ ግንባታ ተጠናቆ ሁማምና ልጁ ወደ አዲሱ ቤት ገቡ።

ዛሬ የሁማም ወንድ ልጆች ሁሉም ሰራተኞች የሆኑ ሲሆን ሴቶችም ደግሞ ለትዳር በቅተዋል። ውድ ባለቤቱ ደግሞ በቅርቡ ላትመለስ በሞት ተለይታዋለች። የስድሳ ዓመቱ ሽማግሌ ሁማም በብቸኝነት ከበኩር ልጁ ቤት ኑሮውን ተያያዘው። አዲሱ ቤት ውስጥ አዲሱን ኑሮውን ይጀምር እንጂ ደስታ አላገኘም፣ ከባሏ ቤተሰቦች ርቃ መኖር የምትፈልገው የልጁ ሚስት የጡረተኛውን ሽማግሌ ሰላም ለመንሳት ጊዜ አልፈጀባትም። በውሃ ቀጠነ በየቀኑ ነበር የነገር ማገዶዋን የምትቆሰቁሰው። አንድ አንዴ ሽማግሌው በግል ጉዳዩዋ ላይ ጣልቃ እንደሚገቡ፣ አንድ አንዴ እርሳቸውን ለመጦር እንደማትችል፣ አንድ አንዴ ወደ ልጆቹ በሽታ እንደሚያስተላልፉ፣ አንድ አንዴ የሰለጠነ የኑሮ ዘይቤ እንደማይገባቸው እያነሳች ትጨቃጨቃለች።

ሁማም የሚመገበው ምግብ የቤት ውስጥ ትራፊ ሲሆን ትራፊውም የሚበላው ለብቻው ነበር። ልብሱማ አብሮአቸው መኖር ከጀመረ ወዲህ አንድ ቀን በግቢው ውስጥ ታጥቦ አያውቅም። የጎረቤት ልብሶችን በማጠብ ይምትተዳደር አንዲት አሮጊት ነበረች የምታጥበው። ፍራሹ ከተዘረጋ አንስቶ ተለውጦም ተነጥፎም ተጸድቶም አያውቅም። የበኩር ልጁም ቢሆን አባቱ ጋር የሚገናኘው ትራፊ ምግቡን ሲወስድለት ብቻ ነው። አንድ አንዴ አባቱ ፍራፍሬ፣አታክልት፣ወይም የተሻለ የምግብ አይነት አሰኝቶት ጥያቄ ካቀረበ ከልጁ የሚሰጠው መልስ ‹‹ይኸው ነው ያለው ምግብ... እዚህ እኮ የፈለከውን የምታዝበት ሬስቶራንት የለም።›› አሞት የህክምና ጥያቄ ካቀረበ ‹‹ሀኪም ምን ያደርግልሃል›› የልጁ የተለመደ መልስ ነው።የልጁ ሚስት ለአንድ ጊዜ እንኳን ጎብኝታው የማታውቅ ሲሆን ልጆቹን ሁማም የሚገኝበት ክፍል እንዳይደርሱ ትከለክላቸዋለች።

በመጨረሻም በልጅ ሚስት ያለው የጥላቻ መንፈስ እንደ እሳተ ጎመራ ፈንድቶ ሳባለቤቷ ሁለት አማራጭ አቀረበች ‹‹ከእኔና ከአባትህ አንዳኛችንን ምረጥ! እኔና አባት ከአሁን በኋላ በአንድ ጣራ ስር መኖር አንችልም›› ልጅ የውድ ባለቤቱን ትዕዛዝ ለማክበርና የዛቻውን ምንጭ ለማድረቅ ሽማግሌውን እና በሽተኛ አባቱን ከቤት ማባረር አለበት። ሰዓቱ

ከቀኑ አስር ሰዓት ሲሆን ዝናብና ብርድ የበዛበት የክረምት ቀን ነበር።በዚያው እለት ሽማግሌው በጠና የታመመበት ሰዓት ከባድ ሳል እያስቸገረው ያለበት ወቅት ነው።ቀጥ ብሎ ሽማግሌው አባቱ ወደሉበት ክፍል ገባ። አባቱን ሰላምታ ለመስጠትና ለማናገር ጊዜ አልነበረውም። የተኙበትን ቆሻሻ ፍራሽ በመጎተት ከክፍሉ አወጣቸው። ከክፍሉ ወደ ጎዳና በሚጎትታቸው ጊዜ አባት ቢያለቅሱም ልጅ ግን ከእዝነት ይልቅ ዱላ፣ ከክብር ይልቅ እርግጫ ነበር የለገሳቸው።

ወልደው ያሳደጉትን አባት ለቁርና ለዝናብ ሰጥቷቸው። ወደ ውድ ባለቤቱና ወደ ሞቀው ቤቱ ሲመለስ ታላቅ ድል ተጎናጽፎ የመጣ ያህልነው የተሰማው።እርኩስ ባለቤቱም የሰራውን ጀብዱ በማድነቅ ከአባቱ እርሷን ስለመረጣት አንድ ግሩም ኩባያ ሻይ ሸለመችው። ዝናብ ያበሰበሰውን ፍራሽ ያዩ የመንገድ ሳይ ተላላፊዎች ከበው ከተመለከቱት በኋላ ከፍተው ሳያዩት በአስቃቂሁኔታ የተገደለ ሽማግሌ መሆኑን ያወቃሉ። በጥቆማቸው መሰረት የፖሊስ ቡድን አካባቢ ድረስ በመገኘት ተገቢውን ምርመራ አደረጉ የወንጀሉን ፈፀሚ በቁጥጥር ስር መዋል ጀመሩ። በአባት ግድያ የተከሰሰው የበኩር ልጅ ፍርድ ቤት ቀርቦ የእድሜ ልክ እስራት ተፈረደበት። እንደ ጣኦት የሚያመልካት ባለቤቱም ልጆቹን ሰብስባ ወደ ቤተሰቦቿ

በመመለሷ ቤቱ ወና ቀረ። ቤቱ ለኪራይ ቢቀርብም ገደቢሱን ቤት ለመከራየት የደፈረ የለም።

አስራ ስምንት አመት እስር ቤት የሚቀቀው የበኩር ልጅ ውድ ባለቤቱ በዓመት አንድ ጊዜ ወይም ሁለት ጊዜ ነበር ይምትጠይቀው። ከአስራ አምስት ዓመት እስራት በኋላ በሆነ ፖለቲካዊ አጋጣሚ ለእስረኞች በሙሉ ምህረት ሲደረግ ከቀሪ እስረኞች ጋር የመፈታት እድል አገኘ። የእስር ቤቱ አዛዥ ለባለቤቱ በቀጣዩ ቀን ላይ ባለቤቷ እስር ቤቱን ለቆ እንደሚወጣ ስለነገራት ‹‹ጀግናውን›› በሷን ለመቀበል የመንግስት ሰራተኛ የሆነውን የበኩር ልጇን ይዛ ወደ እስር ቤቱ አመራች። መኪናውን የያዘው የበኩር ልጇ እና እርሷ እስር ቤቱ በር ሲደርሱ አባት ከእስር ቤት ሲወጣ አንድ ሆነ። አባት ልጅ እና ሚስቱን ሲያይ ልጅ አባቱን ተመለከተ።አባቱ ጋር ለመገናኘት የቸኮለው ልጅ ወደ አባት መኪናውን አፈጠናት። ከልጁ ቁጥጥር ውጪ በሆነ መልኩ አባትና መኪና ተጋጩ አባትም መሬት ላይ ወደቀ። በደረሰው አደጋ የደነገጠው ልጅ መኪናዋ ለማቆም አስቦ ፍሬን ለመርገጥ ቢሞክርም አልተሳካለትም ይባስ ብሎ በስህተት ነዳጁን ረገጠው። ሃይል ያገኘችው መኪና በአባት አካል ላይ ተራመደች።ልጅ ከመኪና ወርዶ የአባቱን ህይወት ሊታደግ ቢሞክርም አባቱ የመጨረሻው እስትንፋስ ሲተነፍስ ደረሰበት።

ወደ ሆስፒታል ለመውሰድ ጥረት ቢያደርግም ነፍሱ ግን ወደ ጌታዋ ተጉዛ ነበር። አባት የእጁን ያገኝ ዘንድ በአሰቃቂ ሁኔታ ሞተ።በሰፈሩት ቁና መሰፈር አይቀርም ማለት ይህ ነው።